ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org
ፕሮግራም፥ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ
Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band

# ዜና ዘገባ

**የካቲት 8 ቀን 2006 ዓ.ም.**

## በወያኔ እና በብአዴን ባለስልጣናት መካከል መሀከል የተጀመረው ሽኩቻ ቀጥሎዋል

ከባህርዳሩ የወያኔ ጠቅላላ ጉባኤ በሁዋላ በባለስልጣናት መሀከል ሲካሄድ የቆየው ኩርፊያና መጠላለፍ እስከአሁን ድረስ ውስጥ ውስጡን እየተካሄደ ሲሆን በተለይ በወያኔ እና በብአዴን መሀከል ያለው ሽኩቻ ከሌሎቹ የተለየ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ፡፡

የበአዴን ባለስልጣናትን ከስልጣን የማባረር እና ወደ ዘብጥያ የማጎሩ ተግባር ቀጥሎ ሰሞኑንም አዲስ ክስተት መፈጠሩን ጉዳዩን የሚከታተሉ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ተናግረዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን በወሰደው የማጥቃት ዘመቻ የዜና አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተርና የብአዴን አባል የሆነውን ታደሰ ዝናዬ የተባለውን ባለስልጣን አንስቶ በምትኩ የወያኔን የበረሀ ታጋይ በሆነው በመብርሀቶም ኪሮስ መተካቱን ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

የዜና አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር ሆኖ ለብዙ ዓመታት ሲሰራ የቆየው ታደሰ ዝናዬ ከነበረበት ቁልፍ ቦታ ያለ አንዳች ምክንያት ከስራ ገበታው ታግዶ ያለ ስራ እንዲንሳፈፍ የመደረጉ ጉዳይ በብአዴን ካድሬዎች ዘንድ በስፋት እያነጋገረ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ ብቻ አራት የብአዴን ባለስልጣናት ላይ ከስልጣን እንዲነሱ መደረጋቸውና ባለውፊው ወር ውስጥም ተከታታይ ጥቃት በብአዴን ላይ መፈጸሙ ወያኔዎች ብአዴኖችን አዳክሞ በሙሉ ቁጥጥር ስር ለማዋል የጀመሩት እንቅስቃሴ አካል ነው በሚል ታዛቢዎች ይተቻሉ፡፡

ታደሰ ዝናዬ የተባለው የብአዴን ካድሬ መጀመሪያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህርነት ሲሰራ ከነበረበት ቦታ በበረከት ስምኦን አማካኝነት ተመልምሎ ለሹመት የበቃ ሲሆን መለስ ከሞተ በሁዋላ በብአዴንና በሕወሀት መሀከል በተፈጠረው ሽኩቻ ምክንያት በስራው ላይ በሚደርስበት ጫናና በሚደረግበት ክትትል ደስተኛ እንዳልነበር የጠቆሙት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አሁንም ከስልጣኑ ሲነሳ ምንም ምክንያት እንዳልሰጡት ገልጸዋል፡፡

በደብረጽን የሚመራው የወያኔው ቡድን በረቀቀ ዘዴና አካሄድ ስጋት ናቸው የተባሉትን የብአዴን ሰዎች በተለያዩ ምክንያት እያንሳፈፋቸው ሲሆን ብአዴን እራሱን በነባር መሪዎቹ ለማጠናከር ሲል በጡረታ የተባረረውን

አዲሱ ለገሰን ድንገት ቢያመጣም የወያኔ ባለስልጣኖች ግን በዘዴ ከሕዝብ እይታ እንዲርቅ እና በማሰልጠኛ ጣቢያ ላይ ብቻ እንዲወሰን አድርገውታል፡፡

በረከት ስምኦንንም ቢሆን በአማካሪነት እንዲቀመጥ ተደርጎ ከአደባባይ እይታ እንዲገለል የተደረገ ሲሆን የክልሉ ፕሬዝዳንት ሆኖ ሲያገለግል የነበረውን ዮሴፍ ረታ ከነመኖሩም እንዲረሳ ተደርጎ ከፖለቲካ መገለሉ ይታወቃል፡፡

አሁን ስልጣን ላይ ያሉትና አለሁ አለሁ የሚሉት የብአዴን አባላት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው ደመቀ መኮንን እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ካሳ ተክለብርሀንም ቢሆን በወያኔዎች ግፊት እሳት እና ውጥረት ያለበት ቦት እየተላኩ ለፈተና እየተዳረጉ መሆናቸው እየተስተዋለ ነው።

ባለፈው ሕዳር ወር ወያኔ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ብሎ የሚጠራውን ቀን ለማክበር ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ የብአዴኑ ባለስልጣን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤው ካሳ ተክለብርሀን ወደ ኦጋዴን በተጉዋዘበት ወቅት ከአደጋ ለጥቂት ያመለጠ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የብአዴን ሊቀመንበር እና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው የ ደመቀ መኮንን ጅጅጋ ከተማ አቅራቢያ 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በታጣቂዎች በተሰነዘረ ጥቃት በኦጋጣሚ ሊተርፍ እንደቻለም ምንጮቹ ይናገራሉ፡፡

ብአዴንን ማዳከም ጨርሶም ሎሌ ማድረግ የሚለው የእነ ደብረጽን መመሪያ ተግባር ላይ እየዋለ በመምጣቱ በቅርቡም የአማራ ክልል ፕሬዝዳንት አያሌው ጎበዜን...የፍትሕ ሚኒስትሩ ብርሀን ኃይሉን....የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ዳይሬክተሩ መላኩ ፈንታን....የማዕድን ሚንስትሩዋን ስንቅነሽ እጅጉን...የዜና አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር ታደሰ ዜናዬን ከስልጣን ሲያነሱዋቸው በረከት ስምኦንን በአማካሪነት ስም...አዲሱ ለገሰን የካድሬዎች ማሰልጠኛ ዳይሬክተር በሚል አንሳፍፈው ከጨዋታ ውጭ ማድረጋቸው አይዘነጋም፡፡

## <u>ከበረሀ የመጡ መኮንኖችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የማዕረግ እድገት እና የገንዘብ ሽልማት ሊሰጥ መሆኑ ተጋለጠ፤ ሽልማቱ ግን ተራ የፖሊስ አባሎችን አይመለከትም ተባለ</u>

የወያኔ ቡድን በአሁኑ ሰዓት በፖሊስ ሰራዊቱ ውስጥ በሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ምክንያት የተፈጠረውን ለማርገብ በሚል ሽልማት ሊሰጥ መሆኑ ታወቀ፡፡ በፖሊስ ሰራዊት አባሎች የተነሳው የሙብት ጥያቄ አቅጣጫውን ስቶ ወደ ሌላ ሁኔታ እንዳይቀየር ለማድረግ የፖሊስ መኮንኖቹን ለማግባባት እና ለመደልል ሲባል የማዕረግ እድገት እና የገንዘብ ሽልማት በቅርቡ የሚሰጣቸው መሆኑ ታውቆዋል፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ መኮንኖችን ጨምሮ የፌዴራል ፖሊስ መኮንኖቹን በየምድብ ጣቢያቸው በኩል የማዕረግ እድገት እና የአራት ወር ደሞዝ ቦነስ እንዲሰጣቸው የጸደቀ ሲሆን ይህን ሽልማት እና የማዕረግ እድገት ለመስጠት ደግሞ ሌላ የግብዣ ፕሮግራም እንደተዘጋጀ ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በተለያዩ ግዜያት ከፖሊስ ሰራዊት አባላት የደሞዝ ጭማሪ እና ሌሎች ተዛማጅ ጥያቄዎች በሚያነሱት ምክንያት በተቁዋሙ ከፍተኛ አመራሮች ላይ ከፍተኛ ፍርሀት ጭሮባቸው የነበረ ሲሆን ይህንን ችግር ለመቅረፍ መጀመሪያ መኮንኖቹን ለመያዝ የተደረገ ስልት መሆኑን ታዛቢዎች ይገልጻሉ።

በዚሁ የማዕረግ እና የገንዘብ ሽልማት ጥናት መሰረት ከበረሀ ጀምሮ የመጡ ታጋዮችን ዋነኛ ተጠቃሚ የሚሆኑ ሲሆን ከ20 ዓመት በላይ የሰሩ የአራት ወር ደሞዝ ሳይቀናነስ እንዲሰጣቸው ከ15 ዓመት እስከ 20 ዓመት ድረስ ያገለገሉ ደግሞ የሶስት ወር ደሞዛቸው ሳይቀናነስ እንዲከፈላቸው የተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

ወያኔ በ1983 ዓ.ም አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ከገባበት ግዜ ጀምሮ ሲታሰብ ሁሉም ታጋይ የነበሩት ከ23 ዓመታት በላይ የስራ ዘመናት የሚቆጠር በመሆኑ ዋነኛ ተጠቃሚ እነሱኑ እንዲሆኑ ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

በ1997 ዓ.ም ምርጫን ተከትሎ ሕዝቡን ደጋፊ ለማድረግ በተጀመረው የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታና እደላ የአንበሳውን ድርሻ የወሰዱት የፌዴራል ፖሊስ አባሎች ያውም ከበረሀ የመጡት በሙሉ ከተራ ወታደር እስከ ከከፍተኛ መኮንን ድረስ ያሉት ሲሆኑ በወቅቱ ገንዘብ በብድር ከባንክ ተወስዶ ተሰጥቶዋቸው ሙሉ ክፍያ እንደከፈሉና ቤቶችን እንዲያገኙ መደረጋቸው አይዘነጋም፡፡

በአሁኑ ሰዓትም መኮንኖቹ ጡረታ ሊወጡ በተዘጋጁበት ወቅት መደጎሚያ ይሆናቸዋል ተብሎ በታሰበበት ግዜ የገንዘብ ሽልማቱና ለጡረታቸው እንዲረዳቸው የማዕረግ እድገት እንዲሰጣቸው መደረጉ ስርዓቱ አይን ያወጣ አድልኦ እየፈጸመ መሆኑን ያሳየ ነው ያሉት ምንጮቹ ወጣት የፖሊስ አባሎች ግን በድርጊቱ ያዘኑ ከመሆናቸውም በላይ አንዳንዶቹ ስራ እየለቀቁ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ከፌዴራል ፖሊስ ሌላ በአዲስ አበባ ፖሊሶች ዘንድ ስጋት ያለ በመሆኑ እነሱንም ለማባበል በተመሳሳይ መንገድ የገንዘብ ሽልማት እና የማዕረግ እድገት ለመስጠት በዝግጅት ላይ የሚገኙ ሲሆን የማዕረግ እድገት ለሚሰጣቸው የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን መኮንኖች ግብዣ ድግስ መደረግ የለበትም በሚል ይህደጎ ስዩም የተባለው የህወሀት ሰው መከልከሉን ተከትሎ በከፍተኛ ባለስልጣኖች ዘንድ ውዝግብ መነሳቱ ታውቋል፡፡

ለአዲስ አበባ ፖሊስ መኮንኖች እንደ ፌዴራል ፖሊስ ሁሉ የግብዣ ስነ ስርዓት ተዘጋጅቶ ማዕረጉ መሰጠት አለበት የሚል አቋዋም የያዙት የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ግርማ ካሳና ሌሎች ሲሆኑ ከተቃዋሚ ጋር ለሚያብር የአዲስ አበባ ፖሊስ መኮንን ግብዣ አያስፈልገውም በማለት እየሞገተ የሚገኘው ደግሞ ኮሚሽነር ተብየው ይህደጎ ስዩም መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በስራ ብቃቱ ዜሮ እንደሆነ የሚነገርለት ይሄው የወያኔው ይህደጎ ስዩም ከወያኔ መከላከያ ሰራዊት በአቅም ማነስ ተብሎ በሳሞራ የኑስ ሲባረር የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ተብሎ በሙዋቹ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ እንዲቀመጥ መደረጉን ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ግለሰቡ ኮሚሽነር ሆኖ ከተመደበበት ወቅት ጀምሮ በውጭ ሀገር ተምረው ከመጡ ነባር የፖሊስ መኮንኖች ጋር መግባባት ባለመቻሉ መኮንኖቹ ስራ እየለቀቁ በተለያዩ የዓለም አቀፍ ተቋዋማት እና የኤምባሲዎች ጥበቃ ኃላፊ እየሆኑ ለመስራት መገደዳቸው የሚታወስ ነው።

አሁን በተዘጋጀው የገንዘብ ሽልማቱ መሰረት የወር ደሞዛቸው 4 ሺህ ብር የሆነው 16 ሺህ ብር የሚያገኙ ሲሆን ከዛ በላይ የሆኑት የፖሊስ መኮንኖችም እንደዛው ተባዝቶ እንዲሰጣቸው ተወስኖላቸዋል፡፡

በቅርቡ ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነርነት በተነሳው በኦህዴዱ ወርቅነህ ገበየሁ ምትክ የተተካው የደኢህዴኑ አባል የመዋቅር ለውጥ አመጣለሁ ብሎ ሽብ ረብ ቢልም ግለሰበቡን የበለጠ ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው ዙሪያውን የተለያዩ ተቀጥላ መምሪያዎችን በአዲስ መልክ ፈጥረው ከበረሀ የመጡ የወያኔ አባላትን ማስቀመጣቸው ታውቋል፡፡

## የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ የሰጠውን ውሳኔ የወያኔ ባለስልጣን ሻረው

## ዳኛ የተሳደበው የፖሊስ መኮንን እስራት ቢፈረድበትም ተፈጻሚ ባለመሆኑ ውዝግብ አስነሳ

ከበረሀ የመጣ አንድ መስመራዊ መኮንን ፖሊስ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ችሎትን በመድፈሩ ፍ/ቤቱ የእስራት ቅጣት ቢወሰንበትም በወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣን ትዕዛዝ ከእስር እንዲፈታ መደረጉ ታወቀ፡፡

ሐብታሙ አሰፋ ሐጎስ የተባለው ግለሰብ ችሎቱን በማመናጨቅ እና በመሳደቡ በቂ ማስረጃ ቀርቦበት እራሱም አምኖ የ6 ወር እስራት ቢፈረድበትም በወያኔ ባለስልጣን የዳኛው ውሳኔ ተሽሮ ከእስር ሊፈታ መቻሉ ታውቆዋል፡፡ ትዕዛዙን የሻረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የሆነው የወያኔ ደሳለኝ በርሔ ሲሆን ይህን ውሳኔ ለመውሰዱ ግለሰቡም ከፍተኛው ፍርድ ቤት ዙሪያ ጥበቃ ኃላፊ በመሆኑ ስራው ሊበደል ይችላል የሚል ምክንያት ሰጥቷል፡፡

የልደታ ምድብ ችሎት ዳኛ በደሳለኝ በርሔ እርምጃ በመበሳጨት በዕለቱ ችሎቱን ዘግቶ ወደ ቤቱ የገባ ሲሆን በማግስቱም የስራ መልቀቂያ ያቀረበ ቢሆንም ለግዜው መልስ እንዳልተሰጠውና እንዳውም ስራ ገበታው ላይ ባለመገኘቱ በቢሮው በር ላይ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንደተለጠፈበት ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በፖሊሱ ላይ ዳኛው ውሳኔ መስጠቱና በደሳለኝ በርሔ መሻሩን ተከትሎ ከወረዳ እስከ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድረስ ያሉ ወጣት ዳኞች እና አቃቤ ሕጎች በጉዳዩ ተወያይተው አቁዋም እንዳይዙም ለእያንዳንዳቸው በደብዳቤ አድማ ማድረግ አትችሉም በሚል ማስፈራሪያ እንደደረሳቸው ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ሰሞኑን በፍርድ ቤት ላይ ወንጀል ፈጽሞ ለእስር የተዳረገውን ፖሊስ ውሳኔ ተከትሎ በተወሰደው እርምጃ ወትሮም የወያኔ ቡድን የፍርድ ቤት ነጻነትን ነፍጎ እራሱ በፈለገው መንገድ ብቻ እንዲጉዋዝለት አድርጎ ያወቀረው በመሆኑ በሀገሪቱ ሕግ አለመኖሩንና ብዙ ግዜ ሲነገር የነበረውን እውነታ ያረጋገጠ ነው ሲሉ የህግ ባለሙያዎች በቁጭት ይናገራሉ፡፡

## በጎንደር ከፍተኛ ውጥረት ሰፍኖዋል

## የሁመራ ወረዳ በድንበር መካለል ሰበብ ለሱዳን ሊሰጥ ነው በሚል ሕዝቡ ስጋት አድሮበታል

በኢትዮጵያና በሱዳን ከድንበር መካለል ጋር በተያያዘ መሬት ተቆርሶ ሊሰጥ ነው በሚል በጎንደር ሕዝብ ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ እየተቀሰቀሰ መሆኑ ታወቀ፡፡በጎንደር የሁመራ ወረዳ ሕዝብ ሰሞኑን ባሰማው ተቃውሞ ከዚህ ቀደም በሙዋቹ የወያኔው መሪ መለስ አስተባባሪነት በአሁኑ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ሀሰን ፈራሚነት ለም መሬት ለሱዳን ተቆርሶ የተሰጠ መሆኑን ጠቅሰው አሁን ደግሞ በድንበር ማካለል ሰበብ ሌላ ተጨማሪ መሬት ተቆርሶ ሊሰጥ መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገለጸ፡፡

ባለፈው ወር አጋማሽ ላይ የሻዕቢያው ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ድንገት የስራ ጉብኝት በሚል በሱዳን ዋና ከተማ ካርቱም ተገኝቶ ለሁለት ቀናት ቆይታ አድርጎ በተመለሰ በማግስቱ የወያኔው መሪ ኃይለማርያም ደሳለኝ

በበኩሉ የወያኔ ባለስልጣናቶችን አስከትሎ ከሱዳኑ መሪ አልበሽር ጋር መገናኘቱን  የድንበር መካለሉ ጉዳይ ላይ ውይይትና ስምምነት ማድረጉ ተከትሎ  ሰሞኑን በጎንደር ሰፊ ውጥረት ሰፍኖ እንደሚገኝ ተጠቆመ፡፡

ኃይለማርያም በመራው ልዑካን ቡድን አማካኝነት ተደረገ በተባለው ስምምነት መሰረት በቅርቡ የድንበር መካለሉ ይደረጋል ተብሎ ይነገር እንጂ ወያኔ ከግብጽ ጋር በገባው የፖለቲካ ውጥረት ደጋፊ ለማድረግ የጎንደርን ለም መሬት ቆርሶ ለሱዳን ለመስጠት ምስጢራዊ ስምምነት ሳያደርግ አይቀርም ሲል ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ካለው የድብቅነት ባሕሪይ ተነስቶ አሁን በድንበር መካለሉ ዙሪያ ተደረገ የተባለው ስምምነት ሀገሪቱን ተጠቃሚ የማያደርግ... ዜጎችን የሚያፈናቅል እና ሕልውና የሚያሳጣ ሊሆን ይችላል በሚል ሕዝቡ በከፍተኛ ደረጃ ስጋት ውስጥ ወድቆ እንደሚገኝ ታውቆዋል፡፡

ከኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር አብረው የተጉዋዙት ሁለቱ የወያኔ ባለስልጣን ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሀኖም እና ብርሀነ ገብረ ክርስቶስ ብቻ ከሱዳን የደህንነት ባለስልጣናት ጋር በምስጢር ውይይት እና  ስምምነት የፈጸሙ ቢሆንም እስከ አሁን የስምምነቱ ጉዳይ አለመገለጹ ተከትሎ በጎንደር ሕዝብ ዘንድ ቁጣ የቀሰቀሰ መሆኑ ታውቋል።

ምንም እንኩዋን የወያኔ ቡድን ስለተደረገው የድንበር መካለል ስምምነት ምስጢር አድርጎ ይያዘው እንጂ የሱዳን መንግስታዊ መገናኛ ብዙሃን ተቋሞች ስለ ሁለቱ ሀገራት የድንበር መካለል ጉዳይ በወረቀት ላይ ስምምነት ማድረጋቸውንና በመጪው መጋቢት ወር ውስጥ በመሬት ላይ ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል መሆኑን እየዘገቡ ይገኛሉ፡፡ የድንበር መካለል ጉዳይ የሉዓላዊነት መገለጫ ስለሆነ ከኢትዮጵያ ህዝብ ተደብቆ ከጀርባ የሚደረግ ሴራ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት አንዳንድ ወገኖች እየገለጹ ይገኛሉ።

አንዳንድ የብአዴን ካድሬዎች በበኩላቸው ከዚህ ቀደም በነበሩ ስርዓቶች የመሬት መካለሉ ጥያቄ ሳይነሳ አሁን እኛ ባለንበት ወቅት መነሳቱ የወያኔ እጅ ያለበት ሳይሆን እንደማይቀርና ሆን ተብሎ የአማራን ክልል ለማጥበብ እና ለማሳነስ የተቀነባበረ ሴራ ሳይሆን አይቀርም በማለት እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡

የአማራን ብሔር ተወላጆችን  ቁጥር ለማሳነስ እና መልክዓ ምድሩንም ለማጥበብ የወያኔ ሰዎች ከሱዳን መሪዎች ጋር ምስጢራዊ ስምምነት ያደረጉ መሆናቸውን የተናገሩት የብአዴን ካድሬዎች ክልሉ የአማራ ሆኖ ለድርድር የተላኩት ደግሞ ወያኔዎች መሆናቸው ጥርጣሬያችንን ይበልጥ ያጎላዋል ብለዋል፡፡